**Kinijit North America Association Of Support Organizations (KNAASO)**
**የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር**

**001/08**

ታህሳስ 26 ቀን፣ 2000 ዓ.ም
ጀንዋሪ 5 ቀን፣ 2008 ዓ.ም

# *በመንግስታዊ ቀዶ-ጥገና ድጋፍ ቅንጅትን ለመምሰል መሞከር ግብዝነት ነው*

*የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫ 97 ወቅት ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ግንዛቤ እንዳለው አሳይቶአል :: ማንንና ለምን መምረጥ እንዳለበት ተረድቶአል :: በዚህ ወቅትና የምርጫውን ውጤት መነጠቅ ተከትሎ ያሳየው ቅሬታ፣ ፍጹም ምክንያታዊ የሆነና ከእምነቱ የፈለቀ እንጅ፣ ከስሜታዊነት የተነሳ ጭፍን የሆነ እንቅስቃሴ አልነበረም:: የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከፓርቲዉ ከቅንጅት ጋር ያለው ትስስር የተመሰረተው፣ ቅንጅት በሚለው ስያሜ ወይም በጣት ምልክቱ ላይ ሳይሆን፣ ድርጅቱ እምነቴ ብሎ ባስቀመጠውና ለመተግበር በገባው ቃል ነው::*

*ቅንጅትን የህዝብ ፍቅር ያስገኘለት ተቃዋሚ ሆኖ በመቅረቡ ሳይሆን የተሻለ አማራጭ ሃሳብ በመያዙና ግልጽና ስልጡን መርህ ለመከተል በመቻሉ ነው:: ቀልብ የሚስብ ስምና በቀላሉ ለግንኙነት የሚመች ምልክት በመያዙ ሳይሆን፣ የህዝብ ፍላጎትን ሊያሟላ፣ ጥያቄውን ሊመልስ የሚችል ሃሳብ በማቅረቡ ነው::*

*ይህን ግዙፍ የሆነ የሞራል የበላይነት ያለው ሃሳብ ይዞ መንቀሳቀሱና የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት መቻሉ፣ ይልቁንም በሰላማዊ ትግል ከልብ በማመን ጠንካራ እንቅስቃሴ ለማድረግ መጀመሩ፣ የኢህአዴግ ከፍርሃት የመነጨ ጥላቻ ሰለባ ሆኖአል:: ቅንጅትን ብሎ የተሰለፈውን ዜጋ ቅስም ለመስበር፤ መሪዎቹን በማሰር፣ ደጋፊዎቹን በማሳደድ፣ ቢሮዎቹን በመዝጋት፣ ህዝባዊ ስብሰባ በመከልከል፣ የዜናና ኢንፎርሜሽን ምንጮችን በማፈን፣ ቅንጅትን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ወገቡን አስሮ ይንቀሳቀሳል:: ቅንጅትን ማፈንና ማጥፋት እንደማይቻል ሲገነዘበው፣ ድርጅቱን ማፈራረስ ይችላል ብሎ ያመነበትን ስልት ተከትሎአል::*

*ይህ ስልት፣ ድርጅታዊ፣ አስተዳደራዊና የህግ ሽፋን የተላበሱ ሴራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ለዚህ ደግሞ ወገንተኝነቱን የቀጠለው የምርጫ ቦርድና የኢህአዴግ የፖለቲካ ፍላጎት አስፈጻሚ የሆነው የፍትህ ስርአቱ፤ እንዲሁም ግብዝ የሆኑ፣ ስልጣን የጠማቸው፣ አድርባዮችን ማሰባሰብ ዋና የማፍረስ ስልቱ መሰረት አድርጎታል:: በዚህ ሴራ እራሳቸውን ያሳተፉ፣ ከቅንጅት ጉያ የወጡ ሶስት ሃይሎች ይገኛሉ፣ ሶስቱም የየራሳቸው ጠባይ አላቸው፣ የሚመሳሰሉበት ደግሞ ሶስት ሌሎች መንገዶች አሉ::*

1. *<u>ብልጣብልጥና አድርባይ</u>፣ የቅንጅት የምርጫ ምልክት ይገባኛል ብሎ ለመውሰድ እየሞከረ ያለው ቡድን፣*
   *ይህ ቡድን ቅንጅት ሲመሰረት ጀምሮ ለማፍረስ ጥረት ያደረገ፣ ለቅንጅት ህጋዊ ምስረታ እንቅፋት በመፍጠር ለኢህአዴግ መሳሪያ የሆነ ሲሆን፣ የቅንጅት መሪዎች ሲታሰሩ በኢህአዴግ ጉያ ውስጥ በመደበቅ ሞቆትና ተመችቶት የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው:: የቅንጅትን ደጋፊዎች ለማሳሳት እችላለሁ ብሎ በማሰብ ከማንነት ስርቆት ባልተናነሰ ሁኔታ፣ ምንም ይሉኝታና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በሌለው መልኩ ብልጣብልጥ ለመሆን በመሞከር ቅንጅት የታወቀበትን የጣት ምልክት በምርጫ ቦርድ ድጋፍ ለመቀማት ይሞክራል::*
2. *<u>አድርባይና ስልጣን ጥመኛ</u>፣ የቅንጅትን ስም ይገባኛል ብሎ ለመውሰድ እየሞከረ ያለቡድን፣*
   *ይህ ቡድን የቅንጅት መሪዎች ሲታሰሩ የአዲስ አበባን ከተማ፣ በህዝብ የተመረጡ ከንቲባ በታሰሩበት፣ ምክትል ከንቲባው ባልተሳተፉበት በአቋራጭ ስልጣን ለመረከብ አሰፍስፎ የነበረ ነው:: የታሰሩ የቅንጅት መሪዎችን ከፖለቲካ ጨዋታ ውጭ ለማድረግ በተጠነሰሰው ሴራ፣ ቅንጅትን ያስመዘገበ ሲሆን በወቅቱ የታሰሩት እስኪፈቱ ብቻ የድርጅቱን ስም እንደሚይዝ ቢገልጽም፣ ከተፈቱ በኋላ ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነ አድርባይና ከግርግሩ ለማትረፍ የሚጥር ቡድን ነው::*
3. *<u>አምባገነንና ሙሰኛ</u>፣* ጥቂት የቀድሞ መኢአድ አመራር አባላትን አሰባስቦ ቅንጅት እኔ ነኝ ለማለት የሚሞክር ቡድን፣
   *ይህ ቡድን በሚሊዮን የሚቆጠር የድርጅቱን ገንዘብ በአገር ውስጥና በውጭ ያባከነና ያሸሸ ሲሆን፣ ገበናው እንዳይጋለጥ ያለው አማራጭ ዲሞክራሲያዊ አሰራር በድርጅቱ እንዳይኖርና ሁሉም ጉዳይ ተዳፍኖ እንዲቀር ለማድረግ በሚጥሩ ሙሰኛ ግለሰቦች የሚመራ ሃይል ነው:: አሁንም ፊውዳላዊና*



**766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010 Tel: 202-541-0556 Fax: 202-541-0557**
**E-mail: kinijitna@kinijitna.org www.kinijitna.org**

አምባገነናዊ አሰራርን የሚከተል በመሆኑ ለድርጅቱ ህገ ደንብ የማይገዛ፣ በጭቃ ሹም አመዳደብ ስርአት የሚያምን፣ የግለሰብን ጭራ ተከትሎ የሚንቀሳቀስ ኋላ-ቀር ቡድን ነው:: በቀድሞ ድርጅቱ ስም ተቀባይነት እንደማያገኝ በመገንዘቡ ቡድኑን ቅንጅት ነኝ በማለት የቀድሞ አባላቱን ለማወናበድ ይጥራል::

ከላይ የተጠቀሱት የየቡድኑ ጠባዮች ሲሆኑ አንድ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ደግሞ፤-

1. በቅንጅትና በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ያለው ትስስር መሰረቱ የይዘትና የእምነት መሆኑን አልተገነዘቡም:: የቅንጅት ማንነት መገለጫ የሆኑ ውጫዊ ቅርጾችን በመቀማት፣ ለቅንጅት ህዝብ የሰጠውን ፍቅርና ክብር የሚያገኙ ይመስላቸዋል:: ይህ ግብዝነት ለህዝብ ካላቸው ንቀትና ምንም አይገባውም አያመዛዝንም ከሚል እምነት ይመነጫል::
2. ሁሉም ቡድኖች ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ይሉኝታ ይጎድላቸዋል:: ስለሆነም በምንም ይሁን በምን እራሳቸውን ብቻ ማውጣት ይመርጣሉ፣ ለህዝብ ስሜትና ለትግሉ መቀጠል ብዙም ደንታ የላቸውም:: ለኢህአዴግ መጠናከር ትልቅ ጉልበት ሆነውታል:: በዚህም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ የሚደረገውን ጥረት እንዲጓተት አድርገዋል::
3. ውሸት፣ ተንኮል፣ ቅጥፈት የሰለቸው ህዝብ፤ ቅንጅት ለሚያራምደው ስልጡን ፖለቲካ ሙሉ መንፈሱን የሰጠና እስከመጨረሻው፣ ለቅንጅት ስምና አርማ ሳይሆን፣ ለአላማው ተሰልፎ ትግሉን እንደሚቀጥል አልገባቸውም:: ህግን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀምም ይሁን፣ አስተዳደራዊ ጫና ወይም የአድርባዮች ብልጣብልጥነት ተደምረው የቅንጅትን መንፈስ ሊያጠፉት እንደማይችሉ አልተረዱም::

ከላይ የጠቀስናቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ

1. ኢህአዴግ በቅንጅት መሪዎች የመደራጀት መብት አፈና ላይ የሚያካሂደውን እንቅስቃሴ እንዲያቆም:: በቅንጅት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን እንዲያቋርጥ:: የመናገርና የመሰብሰብ መብቱን በተነፈገው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም እንጠይቃለን::
2. የሰላማዊ ትግል፣ ብቸኛ የስልጣን ውድድር መድረክ መሆኑን እናምናለን:: ለዚህም የቅንጅት አመራር ግንባሩን ሳያጥፍ ይታገላል:: በሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብም ከጎኑ ይሰለፋል:: ኢህአዴግ ግን የሰላማዊ ትግል ማለት፣ እኔ ባሰመርኩት መስመር መሄድ፣ አድርባይ መሆን ብቻ ነው ብሎ ከቀጠለ፣ ያለውን የትግል አማራጭ ማፈኑን እንዲገነዘብና ይህም ለሚያስከትለው ቀውስ ተጠያቂው ኢህአዴግ እራሱ እንደሚሆን ለማሳሰብ እንወዳለን::
3. የቅንጅት መሪዎች ህዝብን ሰብስቦ የማነጋገር፣ ጋዜጣዊ መግለጫ የመስጠት ህገ-መንግስታዊ መብታቸውና ድርጅቱን ህጋዊ የማድረግ ጥረታቸው ላይ የሚደረገው ተጽእኖ እንዲቆም እናሳስባለን::
4. ብልጣብልጦች፣ አድርባዮችና አምባገነኖች ለኢትዮጵያ ህዝብ ያላችሁን ንቀት እንድታቆሙ፣ የኢህአዴግ ሴራ ተዋናይ ከመሆን እንድትታቀቡ፣ ቅንጅትን ለመቦርቦር የምታደርጉትን አጸያፊና አሳዛኝ እንቅስቃሴ እንድትገቱ እናስገነዝባለን::

እነዚህን ስሜቶች ምንም እንኳን ህገ መንግስታዊ መብቱ የታፈነበት የኢትዮጵያ ህዝብ ለመግለጽ ባይችልም፣ ትክክለኛው የህዝብ ስሜት መሆኑን ሁላችሁም ልቦናችሁ ያውቃል:: ምንም አረጋችሁ ምን የኢትዮጵ ህዝብ ከዲሞክራቲክ የቅንጅት አመራር አባላት ጋር በመሆን ትግሉን ይቀጥላል:: ይህንን ለማስተካከል ካልቻላችሁና ከአፍራሽ ተግባራችሁ የማትቆጠቡ ከሆነ ህዝብ አንቅሮ እንደተፋችሁ ይቀጥላል፣ ታሪክም እስከ አጥንታችሁ ድረስ ይፋረዳችኋል:: ምንም ቢሆን ግን የቅንጅትንና የህዝብን ትስስር መበጠስ ግን ከቶውንም አትችሉም::

ቅንጅት ከኢትጰጵያ ህዝብ ጋር በመሆን ትግሉን ይቀጥላል!

## የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር



766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010 Tel: 202-541-0556 Fax: 202-541-0557
E-mail: kinijitna@kinijitna.org www.kinijitna.org